# እረዳቴ ሁን/ኚ

## ጠቃሚ ምክሩን ይማሩ

1. **መፀሀፉን ያዝልኝ/ዥልኝ:** መፅሀፍ እንዴት እንደምንይዝ በማውራት ጀምሩ—የፊት ገፁ ወደ እኛ ዞሮ። የገፆችን አገላለጥን ለልጅዎ አሳዩ። ከዛም መፀሀፉን ዘግታችሁ ለልጃችሁ በመስጠት እንዲሞክር/ድትሞክር አድርጉ።
2. **ቃሉን መጠቆም እርዳኝ/ጅኝ:** እርስዎ እያነበቡ ልጅዎ ጣቱን/ቷን ከግራ ወደ ቀኝ በገፁ ላይ እንዲያንቀሳቅስ/ድታንቀሳቅስ ጠይቁ። ከላይ ወደ ታች በገፁ ላይ መንቀሳቀሱን/ሷን አረጋግጡ። ቀስ በቀስ ስታነቡ ቃላቱን ይጠቁም /ትጠቁም።
3. **ፊደል አሳየኝ/ዪኝ እና ቃል አሳየኝ/ዪኝ:** ልጅዎ በጣቱ/ቷ ፊደል (እንደ "s" ፊደል) እንዲከብ/ድትከብ ጠይቁ። ይሄን በቀላሉ ማድረግ ሲችል/ስትችል ፊደላት ተጣምረው ቃላት እንደሚፈጥሩ አብራሩ። እንደምሳሌ መፅሀፍ ውስጥ ቃል አግኙ እና በጣታችሁ አክብቡበት። ልጅዎ እንዲሞክር/እንድትሞክር ጠይቁት/ቋት!

### ጠቃሚ ምክሩ ለምን አስፈለገ?

*የፅሁፍን ፅንሰ-ሀሳብ* መማር ማለት ልጅዎ መፅሀፍ አያያዝን እና ገፁ ላይ ያሉትን ቃላት አሰራር አውቋል/ቃለት ማለት ነው። ይሄን መማር ጊዜ ሊፈጅ ይችላል ግን አትጨነቁ። በልምምድ ልጅዎ ይገባዋል/ታል!

## ልጅዎን ይጠይቁ

- መፅሀፉን ያዝልኝ/ዥልኝ። የፊት ሽፋን ገፁ የት ነው?
- ገፁን ልትገልጥልኝ/ጭልኝ ትችላለህ/ያለሽ?
- ይሄን ገፅ ማንበብ ለመጀመር አይናችንን የት እናድርግ?
- በጣትህ/ሽ አብሮ መከተል ትችላለህ/ያለሽ?
- ይሄን መስመር ስጨርስ አይኔ ቀጥሎ የት ይሂድ?
- ይሄ ፊደል ይታይሀል/ሻል? ፊደሉ "t" ነው። በዚህ ገፅ ላይ ሌላ 't' ይታይሀል/ሻል? በጣትህ/ሽ ክበበው/ቢው።
- እነዚህ ሦስት ፊደላት ተጣምረው 'she' የሚል ቃል ይፈጥራሉ። እያነበብኩ 'she' የሚል ቃል ስመለከት እነግርሀለሁ/ሻለሁ በጣታችን እንከበዋለን። ዝግጁ ነህ/ሽ?

## በመዝናናት ተለማመዱ

ልጅዎ ለሚወዳቸው/ምትወዳቸው አሻንጉሊቶች የተረት ጊዜ አዘጋጅ/ጂ! ልጅዎ የሚወደውን/ምትወደውን ሁለት ወይም ሦስት አሻንጉሊቶች እንዲሰበስብ /ድትሰበስብ ጠይቁ። አሻንጉሊቶቹን ልክ ተመልካቾች በሚያዩዋችሁ መንገድ አስቀምጧቸው። ለአሻንጉሊቶቹ ተረት እንደምታነቡላቸው እና ልጅዎ ልዩ ረዳት እንደሆነ/ች ንገሯቸው። Tልጅዎ መፅሀፉን በመያዝ ለአሻንጉሊቶቹ ስታነቡ ገፆቹን እንዲገልጥ /ድትገልጥ ጠይቁ። ልጅዎ ዝግጁ ከሆነ/ች ተረቱን ስታነቡ ቃላቱ ላይ መጠቆም ይችላል/ትችላለች። አዝናኝ መጠቆሚያ ስጡት/ጧት—እንደ እንጨት ወይም ባዶ የተጠቀለለ ወረቀት።